
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ገዳማትና አድባራት የሚገኙ ንዋየ ቅድሳት ልዩ ጥበቃ ክብርና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል።




# ንዋየ ቅድሳት

## አዘገጃጀት አጠቃቀምና ምሥጢር

«ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን»

1ኛ ቆሮ.14፥40

በሚሊዮን በለጠ አሰፋ

ጥቅምት 1999 ዓ.ም

ታርሞና ተስተካክሎ በድጋሚ
ኅዳር 2005 ዓ.ም
ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ በሙሉም ሆነ በከፊል መልሶ
ማሳተም በሕግ ያስቀጣል::


© ሚሊዮን በለጠ አሰፋ 1999 ዓ.ም

ንዋየ ቅድሳት አዘገጃጀት አጠቃቀምና ምሥጢር

መጀመሪያ ጥቅምት 1999 ዓ.ም ታተመ
ሁለተኛ ኅዳር 2005 ዓ.ም ታተመ

## መታሰቢያነቷ

የቅድስት ቤተክርስቲያን ቅርስ /ንዋየ ቅድሳትን/ ለመጠበቅ በየገዳማቱ ዋሻ ምሰው ገደል ቦርቡረው ሙሉ ጊዜያቸውን በጸሎት ሲያሳልፉ፤ከተማ ሳያምራቸው ቆሎ ቆርጥመው፣ ዳዋ ለብሰው፣ ውርጭና ገለባ፣ ፀሐይና ወላፈን ሳይበግራቸው፤ በዚያው ህልፈተ ሕይወታቸውን ላደረጉ አባቶች ትሁንልኝ::





www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና

## ከሁሉ በፊት በልዩ ሁኔታ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ::

"በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋና ክብርና ሠላም ያስፈልጋቸዋልና" (ሮሜ 2÷10)

1= ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጽርሐ ጽዮን ዘ/የአ/ኑ/ማኅበር እና የሥነ ጽሑፍና ኅትመት ሥራዎች ክፍል የመጀመሪያዉን ዕትም አንዳንድ ማስተካከያ በማድረግ ውድ ጊዜያቸውን በማረም ላይ አውለዋል፤ በዚህም ታርሞና ተስተካክሎ በድጋሚ ኅዳር 2005 ዓ.ም ታተ መ::

2=የኮምፒዩተር ጽሑፍ ለሠራችልኝ ወ/ሪት ትዕግስት ጃምቦ

3=የመጽሐፉ ሽፋንና ውስጥ ሥዕላትን በማቀናበር "ግ ራፊክስ ዲዛይን" አቶ አብነት አየለ

4=ለባናዊ ማተሚያ ቤት ባለቤትና ሠራተኞች

ምስጋና ክብርና ሠላም ያስፈልጋችኋልና እነሆ!





## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 8 |
| የመጽሐፉ ዓቢይ ዓላማ | 11 |
| **ምዕራፍ አንድ** ንዋየ ቅድሳት | 13 |
| የንዋየ ቅድሳት አዘገጃጀት | 14 |
| የንዋየ ቅድሳት አጠቃቀም | 15 |
| በንዋየ ቅድሳት ላይ የሚደረግ ጸሎት | 16 |
| የንዋየ ቅድሳት ምሥጢር | 17 |
| **ምዕራፍ ሁለት** ታቦት መንበርና መስቀል | |
| ታቦት | 19 |
| መንበር | 23 |
| መስቀል | 24 |
| የመስቀል አይነቶች | 26 |
| **ምዕራፍ ሦስት** መሥዋዕትና ምሥዋዕ | 27 |
| ስንዴና ወይን | 28 |
| ጻሕል | 30 |




www.ethiopianorthodox.org

ጽዋዕ ....................................................... 31
እርፈ መስቀል ....................................................... 32
ዐውድ ....................................................... 33
አጎበር ....................................................... 33
ማኅፈዳት ....................................................... 33
መሶበ ወርቅ ....................................................... 34

## ምዕራፍ አራት አገልግሎት ሰጭ ንዋያተ ቅድሳት

ሰንና ብርት ....................................................... 36
ሜሮን ....................................................... 37
ቀንዲል /ቅብአ ቅዱስ/ ....................................................... 38
ዕጣን ....................................................... 39
ጽንሐሕ ....................................................... 40
ሙዳይ ....................................................... 41
ጧፍና ሻማ ....................................................... 42
መቅረዝ ....................................................... 43
መኮስተሪያ ....................................................... 44
አትሮንስ ....................................................... 44
ሙዳየ ምፅዋት ....................................................... 46
ቃጭል ....................................................... 46
ደወል ....................................................... 47
መቋሚያ ....................................................... 48





## ምዕራፍ አምስት አልባሳት /ልብሰ ተክህኖ

የቀሳውስት ቀሚስ ....................................................... 50
ካባ ....................................................... 51
የቄስ ሞጣሕት ....................................................... 52
ቆብ ....................................................... 52
ጥምጥም ....................................................... 53
ማክበሪያ ....................................................... 53
ፈረጅያ ....................................................... 53
የዲያቆን ቀሚስ ....................................................... 53
ለምድ ....................................................... 54
የዲያቆን ሞጣሕት ....................................................... 54
አክሊል ....................................................... 54
ልብሰ ታቦት ....................................................... 56
መጎናጸፊያ ....................................................... 56
ቀጸላ ....................................................... 56
መጋረጃ ....................................................... 56
ምንጣፍ ....................................................... 57
ድባብ /ጥላ ....................................................... 58
ግምጃ ....................................................... 59
ማህደር ....................................................... 59



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ስድስት የዜማ ዕቃዎች ......60

በገና ......61
መሰንቆ ......63
እምቢልታ ......65
መለከት ......65
ዋሽንት ......66
ከበሮ ......66
ጸናጽል ......68
አታሞ ......70
ነጋሪት ......71

## ምዕራፍ ሰባት ቅዱሳት ሥዕላት ......72

የቅዱሳት ሥዕላት አጠቃቀም ......73

## ምዕራፍ ስምንት ዕቃ ቤት

/ዕቃ ቤት/ የንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ......75
የንዋየ ቅድሳት መደርደሪያና ማጥን ......75
ዋቢ መጻሕፍት ......77




ንዋየ ቅድሳት





www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

በባሕሪው ኀልፈት፤በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት ልዑል እግዚአብሔር በስድስቱ ዕለታት ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ከፍተኛ ክብርና ባለሟልነትን ያደለው ለሰው በመሆኑ «ሰውን በምሳሌያችን ወይም በአርዓያችን እንፍጠር» ዘፍ.1፥26 ሲል የተናገረው አምላካዊ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ይነበባል።

ከፈጠረውም በኋላ በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ንዳ፣ ግዛ፣ዳኝና ቃኝ ሲል ሥልጣን ሰጥቶታል፤ ከአጠቃላይ ፍጥረታትም ላቅ ያለ እንዲሆን አእምሮው የሰፋ፣ የኀሰበ፣ ጥበብንና ማስተዋልን የተላበሰና ለአምላኩ የተገዛ አድርጎታል። የጥበብ ምንጭና የዕውቀት ባለቤት በመሆንም ማምለኪያውንና መገለገያውን በጥበቡ እያዘጋጀ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ሁልጊዜ «ፈቃድህ ይሁን» በማለት ይኖራል።

ለዚህም ነው በዓለም ላይ ትልቁ ፍጥረት ሰው ከእግዚአብሔር በታች ከአራዊትና እፅዋት በላይ ታላቅነቱን የሚያረጋግጥለት አእምሮውን በመጠቀም ለሀገርና ለወገን እንዲሁም ለተተኪው ትውልድ የሚተርፍና የሚኮራበት ትሩፋትን፣ ቅርስንና ታሪክን የሚያወሳና ባሕል የሚያዳብርበት ንዋየ ቅድሳትን ከተለያዩ ነገሮች እያዘጋጀ ያስቀምጣል። የዚሁም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ አገር አገራችን ኢትዮጵያ ናት ቢባል የታሪክ ሽምያ አይሆንም።





በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚኖሩ ሕዝቦች መኖሪያ የሆነችው ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ከታቦት እስከ ከበሮና ጸናጽል ያሉ ንዋየ ቅድሳት መከማቻ አገር ናት። እንግዳ ተቀባይ ክብርት ሀገር በመሆኗም ታሪኳን፣ ባህሏንና ቅርሶቿን ለመጎብኘት ከተለያዩ ሀገራት የሚከማቹባት ሁሉ በዝርፊያና በሽያጭ ውድና ብርቅዬ ቅርሶቻችንን ባህር አሻግረው በተለያዩ ሀገራት ተከማችተው ይገኛሉ። እንዲያውም አሁን ለደረሰበት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ርቀት መረማመጃ ሁነውላቸው በልጽገውና ከብረው በስርቆሽ በተገኘ ንብረት የታሪክ ባለቤት ነን ባዮች ሆነዋል።

ሰውነትን ለሆዳምነትና ለዕለት ጥቅም በማሳወር የሌላውን ታሪክ በመስረቅ ባለ ታሪክ ነኝ ማለትና ታሪክን መቸርቸር ስግብግብነትና ከንቱነት ነው። አልፎ ተርፎም ለጥቃትና መከራ ይዳርጋቸዋል። እሄው በቴሌቭዥን እንደምናየው አደግን በለጸግን የሚሉ አገሮች በጎርፍ በአውሎንፋስ በጦርነት እንዲሁም በመኪና በአውሮፕላን ፣በባቡርና በመርከብ አደጋ ሲደርስባቸው እንመለከታለን።

የሆነ ሆኖ የተወሰዱብንን ቅርሶች ማስመለስና አሁን ያሉትንና አበው አባቶቻችን ያቆዩልንን ንዋየ ቅድሳት በክብርና በጥንቃቄ መያዝና ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ይኖርብናል።



www.ethiopianorthodox.org

ይህም ሲሆን በቤተክርስቲያን ያሉ ንዋየ ቅድሳት ምሥጢር ያላቸው ስለሆኑ ይዞታቸውም ሆነ መልካቸውን መቀየር ጥሩ አይደለም::በስፋታቸው፣በጥበታቸው፣በብዛታቸው፣በዓይነታቸውም ሆነ በተለያዩ ረገድ ምሳሌ ያላቸው ስለሆኑ ጥንቃቄ ያሻቸዋልና ሁሉም ነገር በማስተዋል ቢሆን መልካም ነው::





# የመጽሐፉ ዓቢይ ዓላማ

1. ንዋየ ቅድሳትን ከማዘጋጀታችን በፊት አዘገጃጀቱን፤ ከአዘጋጀን በኋላ አጠቃቀሙና ምሥጢሩን እንድናውቅ ከተዘጋጀበት ገዝተን የምንጠቀም ወይም መባ የምናቀርብ ከሆነም አውቀንና ተረድተን እንድንፈጽም::

2. ምዕመናንና ምዕመናት ለቤተክርስቲያን የሚያቀርቡት መባ /ስዕለት/ ንዋየ ቅድሳትን ነው:: እናም ምዕመናን ሲያቀርቡ ዕጣን ከሆነ ዕጣንነቱን እንጂ ጥራቱን አይመለከቱም ዘቢብ ቢሆንም እንዲሁ የተበላሸና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንኳን ሲውል ለምንም ነገር የማይጠቅም ያቀርባሉ::
 በተጨማሪም እኼንና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት ለምሳሌ ዕጣን ፣ ዘቢብ፣ ሻማና ጧፍ የመሳሰሉትን ብዙውን ጊዜ በየሜዳው አቧራ ላይ ስለሚገኙ አያያዛቸው ያማ ረ አይደለም:: ይህ ሲባል ንፅህና አይጠብቁም ማለት ብቻ ሳይሆን ክብርንም አይጠብቁም:: ምክንያቱም በአገልግሎቱ ላይ አሉታዊ የአመለካከት ተጽዕኖ ስለሚኖራቸው ነው::

3. ንዋየ ቅድሳቱ ማን፣ ለየት፣እንዴት፣ሊጠቀምባቸውና ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ክብር ተገንዝበን በድፍረትም ይሁን ባለማወቅ ያለ ማዕረጋችን ከመንካትም ሆነ በነሱ ከመገልገል ተቆጥበን በክብና በጥንቃቄ እንድናኖር::



www.ethiopianorthodox.org

4\. ማንኛውም ክርስቲያን ኃላፊነቱን አውቆ የተረከበውን ቅርስ ጠንቅቆ በመገንዘብ አጥብቆ እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ ነው።

5\. ይህችን መጽሐፍ ያነበበ ወይም ቋንቋውን ሳያውቅ ቀርቶ በአስተርጓሚ ያስነበበ ኢትዮጵያዊ ሆነ የሌላ አገር ሰው ንብረታችንና ክብራችንን አውቆ ንዋየ ቅድሳቱን እንዳይነካና እንዳይዘልፍ፣እንዳይዘርፍም የወሰደውም ካለ በክብር እንዲመልስ ጭምር ነው።

ይህ ሁሉ እንዳይሆን ምዕመናኑ ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ቢያነቧትና ቢገነዘቧት የቤተክርስቲያናችንን ትክክለኛ ንዋየ ቅድሳት አውቀው እና መርምረው ያቀርባሉ።





# ምዕራፍ አንድ

## ንዋየ ቅድሳት

ንዋየ ቅድሳት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ይህ ሐረግ የሁለት ቃላት ጥምር ስለሆነ በተናጠል እንመልከት።

**ንዋይ:-** ማለት ገንዘብ ፣ጥሪት፣ቅርስ፣ /ወርቅ፣ብር፣ከብት ሌላም ንብረት/ ይህም ማለት ከሃገር፣ከእንጨት፣ከማዕድን፣ከብረት፣ከጭቃ፣ከቁርበት ከሌላም ሁሉ መልክና ቅርጽ ጌጥም ኖሮት የሚዘጋጅ ነው። ወይም እንዲሁ በራሱ ጥሬ ዕቃ ከንብረት ይቆጠራልና ይህም ንዋይ ይባላል።

**ቅድሳት:-** ማለት ደግሞ ቅድስና ክብር ንጹሕ ጸጋ ያላቸው የእግዚአብሔር የሆኑ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ማለት ነው። «እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል» ዕብ.12÷10

**ንዋየ ቅድሳት:-** ከተመረጡ የተመረጠ ከተለዩ የተለየ ለዘለዓለም ስሙ የሚኖርበት ምርጥ ዕቃ ማለት ነው።

ይህም ስለሆነ ነው ዕቃው ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ተባርኮና ተፀልዮበት የሚገባው፤ ከቡራኬ በኋላ ግን ተራ ዕቃ የነበረው ንዋየ ቅድሳት ሆኖ ለቤተመቅደስ የአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ የክብር ዕቃ በመሆን በማንም የማይነካ ይሆናል።



www.ethiopianorthodox.org

«በተቀደሰው በንዋየ ቅድሳቱ ቤተመዛግብት ሁሉ ላይ ተሾመው ነበር» 1ኛዜና. 26፥26

«ደግሞም ለእግዚአብሔር ቤት አደባባዮችና በዙሪያው ለሚሆኑ ጓዳዎች ለእግዚአብሔር ቤት ለሚሆኑ ቤተ መዛግብት **ለንዋየ ቅድሳቱም** ለሚሆኑ ቤተ መዛግብት በመንፈሱ ላሰበው ሁሉ ምሳሌን ሰጠው» 1ኛዜና. 28፥12

ንዋየ ቅድሳት በአጠቃላይ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች የሚጠሩበት ስም ነው፡፡

## የንዋየ ቅድሳት አዘገጃጀት

ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ የመገልገያ ዕቃዎችን ለማዘጋጀት በቅድሚያ የሚሠሩበትን ነገር ማወቅና መምረጥ ያስፈልጋል፡፡

ከንዋየ ቅድሳት ሁሉ የከበረ ታቦት ነው፡፡ ታቦት ደግሞ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ከማይነቅዝ እንጨት እንዲቀረጽ ታዟል፡፡ ዘጸ.25፥1-9

«እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ የሚያምረው ሰው ሁሉ መባ ተቀበሉ፡፡ ከእነርሱም የምትቀበሉት መባ ይህ ነው፡፡ ወርቅ ፣ብር፣ነሐስ





ሰማያዊና ሐምራዊ ቀይም ግምጃ ፤ጥሩ በፍታም የፍየል ጠጉር የአውራ በግ ቁርበት የማራርም እንጨት የመብራትም ዘይት ለቅብዓት ዘይትና ለጣፋጭ ዕጣን ቅመም መረግድም ለኤፉድና ለደረት ኪስ የሚደረግ ፈርጥ በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ እኔ እንደማሳይህ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት፡፡»ዘጸ.25፥1-9

ካለ በኋላ ገዞት ብሎ ዘጸ. 25፥10 ላይ ከማይነቅዝ እንጨት ታቦት እንዲሰራ ሲያመለክት

«ከግራር እንጨት ታቦት ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን፡፡»ዘጸ. 25፥10 በማለት አዟል፡፡

እንግዲህ ንዋየ ቅድሳትን በምናዘጋጅ ጊዜ ከማይነቅዝና ከጠንካራ ነገር መሆን ይኖርበታል፡፡

የንዋየ ቅድሳቱን አዘገጃጀት ከምንና በምን እንደሚሠሩ በዝርዝርና በሥዕላዊ መግለጫ በዚህ መጽሐፍ በየምዕራፉ ይገኛሉ፡፡

## የንዋየ ቅድሳት አጠቃቀም

ንዋየ ቅድሳት ቀደም ሲል እንዳየነውና ከቃሉም እንደምንረዳው ለአምላካችን ለልዑል እግዚአብሔር የአምልኮት ሥርዓት በምናከናውንበት ጊዜ ሁሉ የምንገለገልባቸው የተቀደሱ ዕቃዎችናቸው፡፡ስለሆኑም ስንጠቀምባቸው በቤተ መቅደስ



www.ethiopianorthodox.org

መሆን አለበት:: ከዚህ አልፎ በመኖሪያ ቤታችንና በረከሰ ቦታ ሁሉ የምንጠቀም ከሆነ የተቀደሰውን ቅዱስ ስሆነ እግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ ለርኩሽና ለኃጢአት ሥራ ሲሆን ነውና እንጠንቀቅ::

ዕጣን ለጸሎት ማሳረጊያና ለቅዱሳት ሥዕላት ማጠኛ መሆኑ ቀርቶ ለቡና ረከቦት የምናጤስ ከሆነ የተቀደሰውን ነገር ለሰይጣን አደረግን ማለት ነው፤ በገና ከበሮና ሌሎችን ማመስገኛ የዜማ ዕቃዎች ለአምላካችን መመስገኛ መሆኑ ቀርቶ ለዘፈን ብንጠቀመው አሁንም ለኃጢአት ሥራ ተ ጠቀመናልና እናስተውል:: የንዋየ ቅድሳቱን አጠቃቀም በተ መለከተ በተናጠል የእያንዳንዱ በየርዕሱ በሚቀጥሉት ምዕ ራፎች ተዘርዝረዋል::

## በንዋየ ቅድሳት ላይ የሚደረግ ጸሎት

በንዋየ ቅድሳት ላይ ሁሉ ጸሎት ማድረግ ተገቢ ነው፤ ይኸ ም ካህናት «እግዚአብሔር አምላክነ ኄር ወመሐሪ ወቅዱስ...» የሚለውን ጸሎት ይጸልያሉ::

ጸሎት ላዕለ ማሕፈዳት ፤ጸሎት ላዕለ ጻሕል፤ጸሎት ላዕለ ጽዋዕ፤ ጸሎት ላዕለ ዕርፈ መስቀል፤ ጸሎት ላዕለ መሶበ ዘወርቅ የሚባሉ ጸሎቶች አሉ እነርሱን ሁሉ በተጠቀሱት ንዋያተ ቅድሳት ላይ በተራ በተራ ይጸልያሉ ::





ንዋያቱ በተደረገው ጸሎት ይከብራሉ:: ካህናቱ ይኼን ጸልየው ካበቁ በኋላ በየመልካቸው ያስቀምጣሉ፤መንበሩን ፣ ጻሕሉንና ጽዋውንም ያለብሳሉ /ያጎናጽፋሉ/ ንዋያቱን ሲያስተናብሩ:- «እግዚአብሔር ማዕመረ ልብ ዘኩሉ ለለአሐዱ...» የሚለውን ጸሎት ይጸልያሉ:: ደግሞም ካህናቱ ንዋየ ቅድሳቱን ሲያለብሱ ወይም ራሳቸው ልብሰ ተክህኖ ሲለብሱ የሚጸልዩት ጸሎት አለ:: በእያንዳንዱ ንዋየ ቅድሳት ላይ የሚጸለየው ጸሎት ከተ ፈፀመ በኋላ ንዋየ ቅድሳቱን ያስተናብራሉ:: አዘጋጅተው ከፈጸሙ በኋላም ባርከው ከዳዊት መዝሙር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን መስዋዕቱን የሚመለከቱትን ተጠቃለው ቀርበዋል:: ለምሣሌ:-«ሃሌ ሉያ ወአንሰ በብዝኀ ምሕረትከ እበውዕ ቤተከ» የመሠዋትን ይጸልያሉ:: ፍሬ ቅዳሴው በየጊዜ ው የሚለወጥ ሲሆን ይህ ግብዐተ መንጦላዕት የተባለው የጸሎት ክፍል ግን በማንኛውም ዕለትና ሰዓት አይለወጥም:: /ትምህተ ክርስትና/


## የንዋየ ቅድሳት ምሥጢር

ምሥጢር ማለት ሰው ሳያውቀው እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው መንገድ የሚከናወን ረቂቅ ሥራ ማለት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በተ መላለሰበት ጊዜ ሲያስተምር በምሳሌ ነበር:: ይኸውም ሁሉም እንደሚገባው በሚያውቀው ነገር እየመሰለ ያስተምር



www.ethiopianorthodox.org

ነበር፤ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ንዋየ ቅድሳትም በምሥጢር የከበሩ በምሳሌ የተነገሩ ናቸው። የንዋየ ቅድሳት ምሥጢር ወይም ምሳሌ በዝርዝር ተጽፏል። አንብቦ ምሥጢሩን መረዳት የእኛ ድርሻ ነው።







# ምዕራፍ ሁለት

## ታቦት፣ መንበርና መስቀል

ምንም ቅዱሳን ንዋያትን ማበላለጥ የሚከብድ ቢሆንም የቤተክርስቲያናችን ሊቅ አድማሴ ጀምበሩ ለከሀዲያን መልስ ይሆን ዘንድ /ትክሌ ሃይማኖት/ በሚል ርዕስ ካዘጋጁት መጽሐፋቸው ከንዋየ ቅድሳት ሁሉ በላይ ታቦት እንደሆነ አስነብበውናል ስለሆነም ከንዋየ ቅዱሳት ሁሉ አስቀድመን ታቦት መንበርና የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር መስቀል እንመለከታለን።

## ታቦት

ታቦት፡- ማለት በብሉይ ኪዳን (በኦሪት ዘመን) የጽላት ማደሪያ ነው፤ ጽላት ማለት ደግሞ ከዕብነ በረድ ቀርጾ አሥርቱን ቃላት በውስጡ ጽፎ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ንዋየ ቅድሳት ነው።

ታቦትና ጽላት በሐዲስ ኪዳን አንድ ሆኖ ተቀርጾ ታቦት፣ጽላት እየተባለ ይጠራል /መሠዊያ/ በመባልም ይጠራል፤ ጽላት ሲቀረጽ ጻሕል ጽዋዕ እንዲይዝ ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር እንዲቻል ተደርጎ ይቀረጻል፤ በጽላቱ ላይም «አልፋ ወኦ ቤጣ የውጣ» የሚለው የጌታችን ስም ይቀ ረጽበታል ከላይ ሥዕለ ሥላሴ ፣ ዝቅ ብሎ ሥዕለ ስቅለት ፣ በቀኝ ምስለ ፍቁር ወልዳ ፣ በስተግራ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ፣



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም መቅደሱ የተሠራለት ጻድቅ ሆነ ሰማዕት ሥዕሉ ይቀረጻል ስሙም ይፃፋል።

ጽላተ ኪዳኑም ማኅደረ እግዚአብሔር ነው፤ ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም። /ሥርዓተ ቤተክርስቲያን/

«በታቦቱ ውስጥ እኔ የምሰጥህን ምስክር ታስቀምጣለህ» ዘጸ. 25፥16-17

«የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ እኔም የምሰጥህን ምስክር በታቦቱ ውስጥ ታኖረዋለህ በዚያም ከአንተ ጋር እገኛለሁ የእስራኤል ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፤ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው ሁለት ኪሩቤል መካከል በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ።»ዘጸ.25፥21-22

«እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ እኔ ወደ ተራራው ወጣ በዚያም ሁን እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁትን ሕግና ትዕዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ አለው።» ዘጸ.24፥12

«እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው» ዘጸ.31፥18

«እግዚአብሔርም ሙሴን አለው ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደ ፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ በሰበርካቸው በፊተኞቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ።» ዘጸ.34፥1-2

«ኢያሱም ካህናቱን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ





በሕዝቡ ፊት እለፉ ብሎ ተናገራቸው ቃል ኪዳኑንም ታቦት ተ ሸክመው በሕዝቡ ፊት አለፉ» ኢያሱ 3፥3-6

«ፍልስጥኤማውያንም የእልልታውን ድምፅ በሰሙ ጊዜ በዕ ብራውያን ሰፈር ያለው ይህ ታላቅ የእልልታ ድምፅ ምንድ ነው? አሉ የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ሰፈር እንደ ገባ አስተ ዋሉ።1ኛሳሙ. 4፥6-7

«የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን።»2ኛ ቆሮ.6፥16


«በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ።» ዕብ.9፥4-5

«በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ መብረቅና ድምፅም ነጎድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።» ራእይ 11፥19

«አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት» መዝ. 131፥18



www.ethiopianorthodox.org



<u>ስለ ታቦት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>

| | |
|---|---|
| ዘጸ. 40÷20-21 | ዘዳ. 4÷13 |
| 2ኛሳሙ. 6 | ዘጸ. 5÷22 |
| 1ኛነገ.8 | 2ኛዜና. 35÷3 |






# <u>መንበር</u>

**<u>መንበር ማለት</u>**:- ማረፊያ መቀመጫ መኖሪያ የተለየ ከፍ ያለና የተከበረ የጽላት ማስቀመጫ ነው፡፡ ጽላቱ እንደ ታቦት በመንበር ይቀመጣል፡፡

መንበር የእመቤታችን ምሳሌ ነው፡፡ እመቤታችን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማህፀኗ ተሸክማ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይታለች፡፡





www.ethiopianorthodox.org

# መስቀል

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ከመሰቀሉ በፊት መስቀል የወንጀለኞች መቅጫ ነበር።


በአሪት ሥርዓት መስቀል ርጉማን ውግዚን የሚሰቀሉበት /የሚቀጡበት/ ነበር ኋላ ግን እርግማናችንን ሽሮ ጌታችን ስለ ተሰቀለበት የነፃነታችን አርማ ሆኖ ኃይላችንና መዳኛችን ይሆን ዘንድ ተሰጥቶናል። ስለዚሁም ቅዱስ ጳውሎስ «ላላመኑት ሞኝነት ለእኛ ላመንበት ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» ሲል አስረድቶናል።/1ኛቆሮ. 1፥18/

በቤተክርስቲያን ብዙ ዓይነት የመስቀል ማዘጋጃ /መሥሪያ ቁስ/ አለ እሱም እንጨት ፣ ወርቅ፣ብር፣ነሐስ፣መዳብና ብረት ይገኝ ብታል።

መስቀል ከእንጨት መቀረጹ ጌታችን የተሰቀለበት ስለሆነ፣ የወርቅ መስቀል ደግሞ ወርቅ ንጹህ ነው ጌታችን አምላካችን ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ስለሆነ ነው፣ የብር መስቀል በአስቆሮቱ ይሁዳ አማካይነት ሠላሣ ብር ለመሸጡ ምሳሌ ነው፣ የነሐስ መስቀል የብሩህነት ምሳሌ ነው። የመዳብ መስቀል የአማናዊ ደሙ ምሳሌ ሲሆን የብረት ደግሞ የተቸነከረበት ችንን የተ ወጋበት ምሳሌ ነው።









www.ethiopianorthodox.org

## የመስቀል አጠቃቀም በአምስት ክፍለን እንመለከታለን

1.የመጾር መስቀል መቀደሻ ከቅዳሴ በኋላ ዲያቆኑ አድንኑ እንዳለ ካህኑ ምዕመናንና ምዕመናትን የሚባርኩበት ፣

2.በንዋየ ቅድሳት ላይ በሥዕል በጥልፍና በቅርጽ የሚዘጋጅ መስቀል፣

3.ካህናት የሚይዙት መባረኪያ (ማሳለሚያ) መስቀል፣

4.ምዕመናንና ምዕመናት በአንገታቸው በማዕተብ የሚያስሩት መስቀል፣

5.በቤተክርስቲያንና በቤተልሔም ጉልላት ላይ እንዲሁም በመቃብር ላይና በመሳሰሉት የሚሰቀል መስቀል ናቸው::

## የመስቀል ዓይነቶች

በመስቀሉ ክብርና አጠቃቀም ሲባል የተለያዩ ቅርጽ እየያዘ ይዘጋጅ እንጂ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ሲል የተሰቀለበት ዕፀ መስቀል አንድ ነው:: በዚህ ርዕስ የመስቀል ዓይነቶች ተብሎ የተገለፀው ለአጠቃቀምና ክብር ሲባል ነው::

| | |
|---|---|
| 1ቀራንዮ ሐዋርያ መስቀል | 7.ልሳነ ከለባት መስቀል |
| 2.ቀርነ በግዕ መስቀል | 8.ትእምርተ ንትፌት መስቀል |
| 3.አርዌ ብርት መስቀል | 9.ሐረገ ወይን መስቀል |
| 4.ዕፀ ሳቤቅ መስቀል | 10.ዓመደ ዓለም መስቀል |
| 5.ዕፀ ሰርናይ መስቀል | 11.ትእምርተ ከዋክብት መስቀል |
| 6.ጽጌ ዳንገላ መስቀል | 12.እሳተ ገቡእ መስቀል |
| | 13.ለንጊኖስ መስቀል |





# ምዕራፍ ሦስት

## መሥዋዕትና ምሥዋዕ

**1=መሥዋዕት:-**በቀድሞው ዘመን ለመሥዋዕትነት የሚቀርበው የእንስሳት ወይም የአዝርዕት ውጤት ነበር፤ ይህም ሥርዓት ከታላቁ አባት ከአዳም ጀምሮ በእነኖህ፣ በእነአብርሃም በእነያዕቆብ በእነሙሴ እንዲሁም እስከ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለድ ድረስ ሲሠራበት ቆይቷል:: አሁን ግን በክርስቶስ ሥጋና ደም መሥዋዕትነት ሰው ሁሉ ዘለዓለማዊዉን ቁርባን ማግኘት ችሏል:: ይኸውም ቀሳውስት በቅዳሴ ጊዜ የሚያቀርቡት ኅብስትና ወይን በመለኮታዊ ምሥጢር ተለውጦ የጌታችን አማናዊ ሥጋና ደም በመሆኑ ነው:: «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ::» ዮሐ. 6፥35

«ሥጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘለዓለም ሕይወት የለውም::» ዮሐ.6፥53-54

«ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::» «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ከልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው:: እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው»ዮሐ.6፥51-59 «ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ቆርሶም እንካችሁ ይህ ሥጋዬ ነው ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ



www.ethiopianorthodox.org

ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ኃጢአት ማስተሰረያ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው::/ማቴ. 26÷26-29

## ሀ.ስንዴና ወይን

ሁሉን ማድረግ የማይሳነው ክሃሊ ጌታ «ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንስሳት መርጦ ለታቦት» እንዲባል ሁሉ፡- ከአዝርዕት መካከል ስንዴንና ወይንን መርጦ በጸሎት ተባርኮ ሥጋና ደም እንዲሆኑ አድርጓል::

«በልቤ ደስታ ጨመርክ ከስንዴ ፍሬ ከወይን ከዘይትም በዛ»መዝ.4÷6


«መልከ ጼዴቅ በወይን በስንዴ ያመጥ ነበር»ዘፍ.14÷18 /ዕብ. 7÷1-3

ለቁርባን /ለመሥዋዕት/ የሚቀርብ ሥንዴና ወይን በወቅቱ የደረሰ፣ወፍ ያልጠረጠረው ዋግ ያላገኘውና ነቀዝ ያልበላው ሆኖ በጎተራ ወይም በማከማቻ ሥፍራ ያልከረመ መሆን አለበት::

ኅብስቱ ለመሥዋዕት ሲዘጋጅ ያላረረ ሆኖ በላዩ ላይ አሥራ ሦስት መስቀል ባለው ማህተም ታትሞ ይዘጋጃል፤ ወይኑም ለመሥዋዕት ሲዘጋጅ ደረቅ ያለ /ቋንጣ/ ሆኖ ንጹህ መሆን አለበት የሚጨመረው ውሃ ከሲሶ (1/3) የበለጠ መሆን የለበትም::







ምሥጢሩ:-ስንዴ የስብ ሥጋን ወይኑ ትክስ ደምን ይመስላሉ

### ስለ ወይን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ. 14÷18 | ሕዝ. 17÷6 | ኢሳ. 16÷10 |
| ዘኁ. 6÷3 | አሞጽ. 9÷13 | ኢሳ. 1÷8 |
| ዘኁ. 13÷23 | 1ኛሳሙ 25÷18 | ኢሳ. 5÷1-2 |
| ማቴ. 9÷17 | ማር. 12÷1 | ዮሐ. 15÷2 |
| ዘሌ. 25÷3-5 | ዮሐ. 2÷6 | |

### ስለ ስንዴ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ. 9÷32 | ማቴ. 13÷25-30 | ማቴ. 3÷12 |
| ዘጸ. 34÷22 | ሉቃ. 22÷31 | የሐ/ሥራ 27÷38 |
| ዘዳ. 8÷7-9 | ዮሐ. 12÷24 | መዝ. 80 (81)÷16 |



www.ethiopianorthodox.org

**2=ምሥዋዕ:-**ምሥዋዕ ማለት ሥጋውና ደሙ ማቅረቢያ ነው። ለእግዚአብሔር መሠዊያ ምርጥ ዕቃ ነው።

**ሀ.ጻሕል:-** ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስና ከብረት የሚሠራ ጎድጓዳ ወይም ዝርግ ወጭት /ሳሕን/ ነው። ጻሕል የኅብስቱ ማስቀመጫና ማክበሪያ ሆኖ ልዩ ክብርና ምሥጢር አለው።

**ምሥጢሩ:-** ጻሕል የእመቤታችን ምሳሌ ነው ፤ እመቤታችን

-ጌታን በማህፀኗ የመሸከሟ ምሳሌ ነው፤ ጌታችን የተወለደበት ግርግም የጻሕል ምሳሌ ነው ተወልዶ አድሮበታልና።

-ጌታችን የተቀበረበት መቃብርም ለጻሕል ምሳሌ ነው። ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት አድሮበታል።

ምሳሌ 25፥11 ማቴ.14፥8 2ኛዜና. 4፥8 ማቴ. 23፥25








**ለ.ጽዋዕ:-**ከወርቅ፣ከነሐስ፣ከመዳብና ከብረት ይሠራል፤ ለመጠጫ የሚሆን በተለይ ለቁርባን ጊዜ የጌታችን ክቡር ደም የሚይዝ የሚከብርበት ምርጥ ዕቃ ነው።

**ምሥጢሩ:-** የእመቤታችን ማህፀን ነው አብሳሪው መልአክ ወደ ድንግል መጥቶ በሚያበስር ጊዜ እርሷም እኔ ድንግል ሳለሁ ይህ እንዴት ይሆንልኛል ባለችው ጊዜ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።» ሉቃ. 1፥35 ሲላት እመቤታችንም «እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይሁንልኝ» ሉቃ 1፥38 ባለችው ጊዜ አካላዊ ቃል በማህፀኗ አደረ የደመ መለኮት ማደሪያ ጽዋውም የማህፀነ ማርያም ምሳሌ ሆኖአል።አካላዊ ቃል በማህፀኗ ተ ቋጠረ፤ ይህም የጽዋው ምሥጢር ነው።

በዕለተ ሐሙስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ «ይኸ በነገው ዕ ለት ለዓለም ድህነት የሚፈሠው ደሜ ነው ሁላችሁም ጠጡት» ማቴ. 26፥27 ብሎ የሠጣቸው ስለሆነ ነው። በጽዋዕ የሚቀርብበትም ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ ኃጢያትና በደል ማስተሠሪያ በዕለተ ዓርብ በዕ ፀ በመስቀል ላይ ደሙን ሲያፈስ መላእክት የሚንጠባጠበውን ክቡር ደሙን የተቀበሉበት ጽዋዕ ስለሆነ ነው።

ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| አስቴር 1፥7 | ማቴ. 20፥22-23 | ራእይ 16፥1 |
| ኤር. 16፥7 | ማቴ. 26፥39 | ራእይ 15፥7 |
| 1ኛዜና.28፥17 | ዮሐ. 18፥11 | ራእይ 5፥8 |
| መዝ 11፥6 | መዝ(22) 23፥5 | |



www.ethiopianorthodox.org


**ሐ. እርፈ መስቀል:-** ማንኪያ፣መቅጃ፣መጨለፊያ ማለት ሲሆን ከወደ እጀታው መስቀል ይኖረዋል:: የሚዘጋጀው ከወርቅ፣ከብር፣ከነሐስ፣ከብረት ከእንጨት ነው:: ነገር ግን ጽዋው ከተሰራበት ቁስ በተመሣሣይ መዘጋጀት አለበት::

እርፈ መስቀል አገልግሎቱ ከቡር ደሙን ለቆራቢያንና ቆራቢያት የሚያቀበሉበት ዕቃ ነው::

**ምሥጢሩ:-** ኢሳይያስ ከንፈሩን ከለምድ የነጻበት ፍህም የያዘ ጉጠት ኢሳ. 6÷6

-ክርስቶስ ጎኑን የተወጋበት ጦር ምሳሌ

-ከወደ መያዣው ያለው መስቀል የጌታችን ደም መስቀል ላይ መፍሰሱን ያመለክታል::







**መ. ዐውድ:-** በቁርባን ጊዜ ጻሕሉ የሚቀመጥበት ዕቃ ነው:: ቅዱስ ሥጋው እንዳይወድቅ /እንዳይነጥብ/ መከለያ ይሆናል:: ዐውድ የሚዘጋጀው ከነሐስ፣ከብረትና ከእንጨት ነው::

**ምሥጢሩ:-** ዐውድ ማለት አደባባይ ማለት ነው፤

-ጌታችን በጲላጦስ አደባባይ የፈረዱበት ምሳሌ ነው::

-በቅዳሴ ጊዜ በሕዝብ ፊት የሚቆመው ዐውድም የዚህ ድርጊት ምሳሌ ነው::

**ሠ. አጎበር:-** ዐውደ ላይ የሚደፋ ከእንጨት ወይም ከብረት የተሰራ ሦስት እግር ያለው ሆኖ አገልግሎቱም ከላይ የሚለብሰው ልብስ ሥጋውን እንዳይነካ የሚከልልና ክብር የሚሰጥ ነው::

**ምሥጢሩ:-** ጌታ ተቀብሮበት የነበረው ማኅተመ መቃብር ምሳሌ ነው::

**ረ. ማኅፈዳት:-** አምስት የልብስ አራፊዎች ሲሆኑ፤ ምሳሌነታቸው እንደሚከተለው:-

1. ዐውዱ የሚለብሰው የእመቤታችን ድንግልና
2. ጻሕል ላይ የሚነጠፈው የሰፋድል(በማህፀን ውስጥ ያለ የህፃን መጠቅለያ
3. በኅብስቱ ላይ ያለው አጎበር ላይ ያሉት ሦስቱ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ናቸው፤ አብ ለማጽናት ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋ በመዋሐድ መንፈስ ቅዱስ ለማንጻት ሦስቱ አድረውበታል::




www.ethiopianorthodox.org

**ሰ. መሶበወርቅ:-** ሕብስቱን ከቤተልሔም ማምጫ ሲሆን አሠራሩም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሸምሸርሸጢን ከሚባል ከማይነቅዝ እንጨት ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ከስንደዶ ሳር ይሠራና ላዩ በወርቀዘቦ ይጌጣል።

ምሥጢሩ:- መሶቡ የእመቤታችን ምሳሌ ነው፤

- ወርቀዘቦው የእመቤታችን ንጽህናዋና የድንግልናዋ ምሳሌ ነው፤
- ሕብስቱ የአማናዊው ወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው፤
- ከቤተልሔም ወደ ቤተመቅደስ የኅብስቱ በመሶበ ወርቅ መሔድ ጌታችን በቤተልሔም ዋሻ ተወልዶ ካደገ በኋላ በሠላሣ ሦስት ዓመቱ ወደ ቀራንዮ ለመሠዋት (ተሰቅሎ ሊሞት) የመሄዱ ምሳሌ ነው።











www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

## አገልግሎት ሰጭ ንዋያተ ቅድሳት

አገልግሎት ሰጭ ንዋያተ ቅድሳት ማለት በቤተክርስቲያን በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ለአገልግሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅዱሳትና ከቅዳሴ ውጭ ሊያገለግሉም የሚችሉ ናቸው:: በዚሁ ተካተዋል በአጠቃላይ እንደሚከተለው ቀርበዋል:-

**1-ሰንና ብርት**:- ከነሐስ፣ከመዳብ፣ከብረት የሚሠራ እንደማንቆርቆሪያ ያለ መታጠቢያ ነው:: እንዳንዴ መቁረሪት ወይም ኩስኩሰት ይሉታል::

ሀ. ሰን:-ውሃ መያገቦው ሲሆን፤

ለ. ብርት:- ማስታጠቢያው ነው::







ምሥጢሩ:- ሰንና ብርት ጲላጦስ «ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ...» ብሎ እጁን የታጠበበት ምሳሌ ነው::

1ኛ ነገሥ. 7፥38-39 ማቴ.27፥24 ዮሐ.ወ 13፥5

**2.ሜሮን:-**ሜሮን ጳጳሳት ከበለሳንና ከዕጣን እንጨቶች ከአስጳዳዮስ ከሊላም ከብዙ ዓይነት ዕፅዋት ሽቱ የሚያወጡት ቅብዓት ነው:: ራእ.18፥13 ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በሁለተኛ የሚገኘው ምሥጢረ ሜሮን ነው::

ሜሮን ከጥምቀት ቀጥሎ የሚቀባ ቅብዓት ነው፤ ይህም ከማይደገሙት ምሥጢራት አንዱ ነው::

ምሥጢሩ:- በብሉይ ዘመን ንዋየ ቅድሳት የሚከብሩት፣ ካህናት ሲሾሙ ነገስታት ሲነግሡ የሚቀቡት ነበር::

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 28፥41 | ዘሌዋ 4፥3 | 1ሳሙ 9፥16 |
| ዘጸ 29፥7-21 | ዘሌዋ 6፥20-22 | 1ሳሙ 10፥1 |
| ዘጸ 40፥9-16 | ዘሌዋ 7፥36 | 1ሳሙ 16፥1-13 |
| ዘሌዋ 8፥2-30 | ዘሌዋ 21፥10-12 | 1ነገ 1፥34-45 |





www.ethiopianorthodox.org

በሐዲስ ዘመን ጥምቀተ ክርስትና ጊዜ ሜሮን እንዲደረግ፤ አዲስ ቤተክርስቲያን፣ አዲስ ንዋየ ቅዱሳት ፣ታቦትም የሚከብረው በቅብዐ ሜሮን ነው::

**3.ቀንዲል /ቅብዓ ቅዱስ/:-**የሚገኘው ከወይራ ዛፍ ፍሬ ብቻ ነው:: ወይራ በአብዛኛው በአገራችን በኢትዮጵያና በውጭ አገር በእስራኤልና በደቡብ አውሮፓ ይገኛል:: ዘይቱ ለመድኃኒትነት ይጠቀማል ይኸውም በካህናት ተፀልዮበትና ተ ባርኮ ለህሙማን ይሠጣል/ይቀባል/

ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በሰባተኛ የሚገኘው ምሥጢረ ቀንዲል ነው፤ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በሰባተኛ የሚገኝ ነው::

ቀንዲል ለታመመ የሚቀባ ቅብዓት ነው:: ይህም ሥርዓት ከሚደገመው ውስጥ ይመደባል::

ምሥጢሩ:- የወይራ ዛፍ በቁመናው የልማትና የብልጽግና ምልክት ነው:: ዘዳ 24÷20 መዝ 128÷3 ሮሜ 11÷17-24

ቅብዓቱ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው::1ዮሐ 2÷20-27

ተጨማሪ ጥቅስ

ዘጸ.30÷22-33 ሚክ.6÷15 ዘኁ.27÷28 ኢሳ.17÷6 ዘዳ.6÷11 ማቴ.21÷1







**4.ዕጣን:-** በበረሃ ከሚበቅል እንጨት የሚለቀም ነው ፤ይህም ለቤተመቅደስ የተዘጋጀ መስዋዕት ሆኖ የሚጤስና የሚታጠን፣ ጸሎት ማሳረጊያ ነው:: መልኩም ነጭ/ጽዓዳ/ የሆነ ሲሆን ይህም ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ዕጣንን የተመላ ሰማያዊ ማዕጠንት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እየሰገዱ ለዓለም ደኅንነት የሚለምኑበት ነው:: ራእይ 8÷3-5 ራእይ 5÷8-9

ካህናት በመንፈቀ ሌሊትና በነግህ ጊዜ በቅዳሴ ጊዜ በየማዕዘኑ ያጥኑበታል:: ቅዳሴውንና ጸሎቱን ወደ እግዚአብሔር ያሳርጉበታል:: ማቴ.2÷11 መዝ 140÷2

ምሥጢሩ:- ፍህሙ የመለኮት ምሳሌ


- ዕጣኑ የቅዱሳን ምሳሌ
- ጢሱ የምስጋናና የጸሎት ነው
- ሽታው /መዓዛው/ በአካባቢው መዳረስ የመልካም ሥራ ውጤት
- የጢሱ ማረግ የቅዱሳን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት መድረሱ
- ጢሱ እንደ ደመና በምዕመናን እና ምዕመናት ላይ ሲያንዣብብ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን በጸሎት ጊዜ እንደሚቀርብ ያስረዳል::





www.ethiopianorthodox.org

**5. ጽንሐሕ /ማዕጠንት/:-** የዕጣን ማጠኛ ዕቃ ነው:: የሚሠራውም ከወርቅ፣ከብር፣ከነሐስና ከብረት ሆኖ ቀርጾና ውበት እንዲኖረው ተደርጎ፤ ማንጠልጠያውና እያንዳንዱ ጌጥ ቁጥሩ ሳይዛባ የተዘጋጀ መሆን አለበት:: ምክንያቱም በአቀጣጫውና በመጠኑ ምሥጢሩ ይገለጻልና::



**ምሥጢሩ:-** ፍህሙ የመለኮት ምሳሌ
- በሦስቱ ሀብሎች መሀል ያለው ሀብል የወልደ እግዚአብሔር
- ይኸው ዘንግ መውረዱና መውጣቱ
  - .**መውረዱ** ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፤
  - .**መውጣቱ** ትንሣኤውና እርገቱ ሲሆን
  - .**እንደገና መውረዱ** ዳግም ምፅዓቱን ያመሰጥራል::
- መያገናው አንድ መሆኑ የአንድነታቸው ምሳሌ ነው::
- በሀብሎቹ ላይ ያሉት ሻኩራዎች/ደቡልቡል ነገሮች ብዛት ቢያንስ 12 ቢበዛ 24 መሆን አለበት::





.12 ቢሆን ሐዋርያት፣
.24 ቢሆን በካህናተ ሰማይ የመሰላል::

-የሻኩራዎቹ ድምጽ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑ መላዕክት ድምጽ ምሳሌ ነው::

-እጣንና እሳት የሚዋሐዱበት ንዋየ ቅድሳት የእመቤታችን ማህፀን ምሳሌ ነው::

-ክዳኑ ላይ ያለው መስቀል በቀራንዮ መሰቀሉ፣ሦስቱ ሀብሎች ከፍህምና ዕጣን ከያዘው ጋር መያያዛቸው እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅዱስት ድንግል ማርያም ማህፀን ሲያድር እግዚአብሔር አብ ለማጽናት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሰርጽባት፤ሁሉም ማደራቸውን የሚያሳይ ምሥጢር ነው::

**ተጨማሪ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ**

| | | |
|---|---|---|
| ዘኁ 16÷16-35 | ዘሌ.10÷1-2 | ዕብ 9÷4 |
| ዘኁ 16÷46 | ዘሌ 16÷12 | ራእ 8÷3-5 |
| ዘኁ 16÷39 | 1ነገ 7÷50 | |
| ዘኁ 4÷14 | 2ዜና 26÷16-20 | |

**6.ሙዳይ:-** መክተቻ ዕቃ በተለይ ለዕጣን /ሙዳዬ ዕጣን/ የሚዘጋጀው ከስንደዶ ሲሆን አገልግሎቱ ለዕጣን ማስቀመጫ ነው:: በቅዳሴ ጊዜ ከሙዳይ ውስጥ አምስት ቆቆር ዕጣን ይቀመጣል::

**ምሥጢሩ:-**ሙዳይ የእመቤታችን ምሳሌ ነው፤በሙዳይ ውስጥ አምስት ራስ ዕጣን መቀመጡ የአምስቱ ኪዳናት ምሳሌ ነው::


ሀ. የቁርባነ አቤል
ለ. የመስዋዕተ ኖህ የሂሩተ አብርሃም
ሐ. የመብአ ይስሐቅ
መ.የተልዕኮ ሙሴ ወአሮንና
ሠ. የመስዋዕተ መልከ ጼዴቅ ናቸው::





www.ethiopianorthodox.org

**7. ጧፍና ሻማ፡-** ከሰምና ከፈትል የሚዘጋጅ ለብርሃን መስጫ መገልገያ ነው።
**ምሥጢሩ፡-** ጧፍና ሻማ የመላእክት ምሳሌዎች ናቸው።
ብርሃኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።
«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» ዮሐ 8÷12








**8.መቅረዝ /ተቋመ ማህቶት/** ከብረት የሚዘጋጅ በድሮ ጊዜ ከእንጨትና ከቀንድ ይበጃል የመብራት መስቀያ መቅረዝ ወይም ተቋመ ማህቶት ይባላል። ጥዋፍና ሻማ ዘይትም ይበራበታል ዘይት ተጨምሮ የሚበራው ቀንዲል ይባላል።

በቤተክርስቲያን ብዙ መብራት እንዲበራ ታዟል፤ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚነበቡበት ጊዜ በጣም ብርሃን እንዲኖር ይፈለጋል፤ በተለይ ወንጌል ሲነበብ የብርሃኑ መጠን ከፍ ያለ እንዲሆን ታዟል /ተወስኗል።
**ምሥጢሩ፡-** መቅረዝ የአካለ ሥጋ ምሳሌ ነው፤
መብራት የዓይነ ሥጋ ምሳሌ ሲሆን፤
ብርሃኑ የምግባርና ሃይማኖት ምሳሌ ነው። (የዓይነ ነፍስ)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 40÷24 | ዘሌ 24÷2-4 | ራእ 1÷12-20 |
| ዘጸ 27÷20-21 | ዘኁ 4÷2 | ራእ 11÷4 |
| ዘጸ 25÷31-40 | ማቴ 5÷15 | |





www.ethiopianorthodox.org

**9. መኮስተሪያ :-** ክብረት የሚዘጋጅ የመብራት ጫፍ ማስተካከያ /ሲጎበጥ ማቅኛ/ ክሩ ተቃጥሎ በአንድ በኩል ሲጎብጥ የሚስተካከልበት ነው፡፡ ዘጸ 25፥38 ነገ 7፥49

**ምሥጢሩ:-** መብራት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፣ ክሩ የአካለ ሥጋ ፣መኮስተሪያ የአካለ መለኮት ፣መኮስተሪያ ሲያቀና በወንጌል መደሻ መምህራንና ሰባኪያን የተሰናከሉትን ሲመልሷቸው ሲያቀርቧቸው፡፡

**10 አትሮንስ /መንበረ መጻሕፍት:-** ከለፋ ቆዳ፣ሸንበቆ፣ቀርከሃ፣ጣውላና ብረት ሆኖ ማቆሚያው ከብረት ወይም ከእንጨት ይዘጋጃል፡፡

የመጽሐፍ ማስቀመጫ ሰባኪያን አንባቢያን መጽሐፋቸውን የሚያስቀምጡበት የቤተክርስቲያን ዕቃ ነው፡፡


አትሮንስ ሲሰራ ቁመቱ ከፍና ዝቅ እንዲ ተደርጎ ይኸውም ለረጅም ሰው አስረዝሞ እንዲጠቀም አጭር ሰው ደግሞ አሳጥሮ እንዲጠቀም ነው፡፡ አብዛኛው ጊዜ ግን በመካከል ሰው ቁመት ተመጥኖ /ፊክስድ/ ይሰራል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አጭር ሰው ከሆነና አትሮንስ ከረዘመበት የእጁን እንቅስቃሴ እንዳያግደው ከአትሮንሱ ወጣ እያለ ቢሰብክ አሊያም ከፍ ሊያደርገው የሚችል ነገር ላይ ቢወጣ መልካም ነው፡፡ ሰባኪው ረጅም ከሆነ ደግሞ አትሮንሱ ከሆዱ ስር እንዳይሆንና ምዕመኑ ትምህርቱን ትተው የሰውየውን ቁመት መርዘም እየተመለከቱ እንዳይዘናጉ ከአትሮንሱ ወጣ ብሎ ሊሰብክ ይገባል፡፡

ነገር ግን በቅዳሴ ጊዜ በሚደረግ ሥብከት መምህሩ ከአትሮንሱ ፍጽም መውጣት የለበትም/አጭር የስብከት ዘዴ/

**ምሥጢሩ:-** አትሮንስ የእመቤታችን ማህፀን ምሳሌ ሲሆን በላዩ ላይ ያለው መጽሐፍ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡










www.ethiopianorthodox.org

**11.ሙዳየ ምጽዋት:-** ከብረትወይም ከእንጨት የሚዘጋጅ የገንዘብ መክተቻ ሳጥን ፤ ምዕመናን አምኀ ቸውን የሚያስገቡበት አፈጠባብ ንዋየ ቅድሳት ነው::2ዜና24፥11 ማር 12፥41



**12.ቃጭል:-** ከብር፣ከነሐስና ከብረት ሊዘጋጅ ይችላል፤ አገልግሎቱ ቅዳሴ ሲገባ፣ በቅዳሴ ጊዜ «ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን...» ሲባል በድርገት ጊዜ /ሥጋ ወደሙ ሲቀርብ/ እና እግዚኦታ ላስ ይመታል::

ምሥጢሩ:- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሐ ግቡ ብሎ መጥምቀ ዮሐንስ በበረሃ የጮኸው ጩኸት በመከራው ጊዜ ያስማው የመራር ኃዘን ድምጽ ምሳሌ ነው:: ማቴ 3፥1-2







**13.ደወል:-** ከጠንካራ ብረት ወይም ብረት መሠል ድንጋይ ይዘጋጃል:: አገልግሎቱ ሊሊት ከሰዓታትና ማኅሌት በፊት በጾም ቀን ስድስት ሰዓት ሲሆን ተጋብኡ ተብሎ ይደወላል፣ ከቅዳሴ በፊት ምዕመናንን ለማነቃቃት አምስት ጊዜ፣ እግዚኦታ ላይ አሥራ ሁለት ጊዜ ይደወላል::


ምሥጢሩ:-ደወል የቅዱሳን ነቢያት ምሳሌ ነው፤ ኖህ በመርከብ በነበረበት ዘመን ጧት /ነግህ/ ቀን /ቀትር/ እና በምሽት /በሠርክ/ ይደውል ነበር::

በአጠቃቀሙ ያለው ምሥጢር ደግሞ:-

-ከቅዳሴ በፊት አምስት ጊዜ ሲደወል አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው::

-ፍሬ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ዲያቆኑ ፃኡ ሲል ሦስት ጊዜ መደወሉ የሥላሴ፤

-እግዚኦታ ላይ አሥራ ሁለት ጊዜ መደወሉ ደግሞ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስብከተ ወንጌል በዓለም መዳረስ ምሳሌ ነው::





www.ethiopianorthodox.org

**14. መቋሚያ:-** ብዙውን ጊዜ ከእንጨት የሚዘጋጅ እንደ ብትር ዘለግ ያለ ከወደ ጫፉ መስቀል ቅርጽ ያለው ነው:: በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የT ፊደል ቅርጽ ያለው አሊያም ድቡልቡል የሆነ ነው፤ ከወደ ጫፉ የሚደረገው ነገር የወርቅ፣የብር፣የነሐስ፣የብረት፣የቀንድና የእንጨት ሊሆን ይችላል::

አገልግሎቱም መደገፊያ፣ መምርኮገርና መዘመሚያ ነው:: ይኸውም ከከበሮና ከፀናጽል ጋር እንዲሁም ብቻውን ማህሌት ላይ በዝማሜና በሽብሸባ ያገለግላል::

<u>ምሥጢሩ:-</u> መቋሚያ የአዳም ተስፋ እና ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በእፀመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: መቋሚያ ያዕቆብ ትእምርተ መስቀል ያለበት በትር በፊቱ እያቆመ ይሰግድና ይጸልይ የነበረበት ምሳሌ ነው::


ካህናት መቋሚያ በትከሻቸው አድርገው ወዲያና ወዲህ ማለታቸው አይሁድ ጌታን በዕለተ ዓርብ መስቀል አሸክመው ወደ ቀራንዮ መውሰዳቸውና ካህናቱ መቋሚያውን ከዜማ ጋር አስማምተው ከመሬት ላይ መጣልና መደሰቃቸው አይሁድ ጌታን «ማነው የመታህ?» እያሉ ተራ በተራ በዘንግ መምታታቸውን ለማስታወስ ነው::

ሌላው ደግሞ መቋሚውን እንደ ማማተብ አድርገው ከትከሻቸው አንሥተው እንደ ማማተብ አድርገው ከትከሻቸው አንሥተው ወደ መሬት ማሳረፋቸው ሌላም ሰው መቀበሉ /መሰብሰቡ/ እናም ማስቀመጡ ጌታችን መስቀል ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲጓዝ ደክሞት ስለነበር ሳንሰቅለውና የልባችን ሳይደርስ ሕይወቱ ያልፍብናል በማለት መስቀሉን ለሌላ ሰው ማሸከማቸውን ለማስታወስ ነው::









www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## አልባሳት

አልባሳት ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ ካህናት ሲቀውንት የሚለብሱአቸው እንዲሁም ንዋየ ቅድሳት ባጠቃላይ የሚጎናፀፉባቸው የሚሸፈኑባቸው ናቸው።

### 1.ልብሰ ተክህኖ

በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ ካህናት በቤተ መቅደስ ሲያገለግሉ የሚለብሱት ልብስ ነው።

ዘጸ 31÷10-11
ዘጸ 39÷29
ዘጸ 28÷40-42

**ሀ. የቀሳውስት ቀሚስ:-** ቀሚስ የሚለው ቃል ከዐረብኛ የመጣ እንደሆነ ይነገራል ይኸም በጥንት ዘመን አብደላከኒ ቀሚስ የሚባል ነበር በዘመናችን ግን ከማንኛውም ጌጥነት ካለው ጨርቅ ይሠራል።

-የሚቀድሱ ካህናት ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ታዟል፤ የሚቆርቡም ምዕመናን ንጹሕ ነጭ ልብስ እንዲጠቀሙ ይገባቸዋል።

-ካህናት ልብሰ ተክህኖ ከመልበሳቸው በፊት በጳጳስ እንዲያስባርኩ ጳጳስ ካልኖረ ራሳቸው ባርከው እንዲለብሱ ተደንግጓል።

-ካህናት የሚለብሱት ልብሰ ተክህኖ እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ መሆን አለበት። ከለበሱትና ምናልባት በጣም ቢረዝምባቸው ማውለቅ የለባቸውም በቀበቶ /በዝናር/ መሠብሰብ ይገባቸዋል እንጂ።





ምሥጢሩ:- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ሠላሳ ሦስት ዓመት ድረስ የለበሳት ሲያድግ በተአምር አብራ ታድግ የነበረችውን ቀሚስ ያመለክታል።

አይሁድ ጌታችንን ለፍርድ ወደ አደባባይ ሲወስዱት ልዩ ልብስ አልብሰውት ነበር ዛሬም ካህናት የራሳቸውን ልብስ ለብሰው መቀደስ አይችሉም ምክንያቱም ጌታ የራሱን ከልጅነቱ አብራ ያደገችውን ልብስ እንደለበሰ አልተሰቀለምና።

**ለ. ካባ:-** መደረቢያ ነው ፤ካባ አምስት መንዲል /ከልጅ/ እንዲኖረው ታዟል። መንዲል /ከልጅ/ ማለት ሰምድ ማለት ነው። የሰምድ ወራጅ እንደላንቃ እየሆነ ስለሚወርድ ካባላንቃ ተብሏል። አሠራሩም የተለያዩ ቀለማት ካላቸው ጨርቆች ነው።ወይም በመካሺ /ወርቀ ዘቦ/ ሊሠራ ይችላል።

ምሥጢሩ:-አምስቱ ሰምድ በአምስቱ አዕማድ ምሥጢርነው።





www.ethiopianorthodox.org

**ሐ. የቄስ ሞጣሕት:-** ቀሳውስት ባንገታቸው አጥልቀው ቀሚሱ ላይ የሚደርቡት ሬት ለሬት የሚወርድ ልብስ ነው:: የሚዘጋጅበትም ጨርቅ ቀሚሱ ከተዘጋጀበት ዓይነት ይሆናል::


**ምሥጢሩ:-** ሞጣሕት የፍኖተ ቅዱሳን ምልክት ነው:: -መርዘሙ ከሬት ለሬት ረጅም መንገድ ይጠብቀሃል አሁን ካሳለፍከው ገና የምታሳልፈው ይረዝማል ለማለት ነው::

**መ. ቆብ:-** መነኮሳትና በሕግ ያሉ ቀሳውስት ቆብ እያደረጉ ይቀድሳሉ እንዲሁም በማንኛውም አገልግሎት ከጭንቅላታቸው አይጠፋም፤የመቀደሻው ግን የተለየ አክሊል የመሰለ ነው:: መሪጌታዎች ጥምጥም ያደርጋሉ::

**ምሥጢሩ:-** በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ አይሁድ የደፉት የሾህ አክሊል ምሳሌ ነው::

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

ዘጸ 28፥40 ዘጸ 8፥9 ዘጸ 29፥6







**ሠ. ጥምጥም /ሰበን ወይም በፍታ/:-** ሰበን የራስ ልብስ፣ጌጥ፣ ሽልማት ፣ጥምጥም ማለት ነው::

/መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ መመዝገበ ቃላት ሐዲስ/
«ንጹህ ጥምጥም በራሱ ላይ አድርጉ አሉ»

ዘካ3፥5

**ምሥጢሩ:-** ቅዱስ ቶማስ ከህንድ ወደ ኢየሩሳሌም በደመና ሲጓዝ እምቤታችን ስታርግ በማየቱ ለሐዋርያት እንዲመሰክር መግነዟ /ሰበኗን/ ሰጠችው እርሱም ለሐዋርያት አካፈላቸው:: - የእመቤታችን ምሳሌ ነው::

**ረ.ማክበሪያ:-** ታቦት ማክበሪያ /ታቦት መሸከሚያ/ ለታቦት ክብር በራስ ላይ አስቀድመው የሚያኖሩት ነው::

**ሰ. ፈረጂያ:-** ከመልከ መልካም ጨርቅ የሚዘጋጅ እጅጌ ሠፊ፣የጳጳስ ቀሚስ ነው::

**ምሥጢሩ:-** ቀሚሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለብሶት የነበረው ሲሆን እጅጌው ሰፊ ፈረጅያ የእጅጌው መስፋት ብዙ መክሊት መቀበላቸውን ያመለክታል::

**ሸ. የዲያቆን ቀሚስ:-** ከላይ የቀሳውስት ቀሚስ በሚል ርዕስ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እንደገና መድገም አያስፈልግም::



www.ethiopianorthodox.org

**ቀ. ሰምድ:-** በጥንት ዘመን ሰምድ ለብቻ ይሠራ ነበር፤ አሁን ግን ሰምድ ከቀሚስ ጋር አብሮ ይሰፋል:: ስለ ሰምድ ከላይ ካባ በሚለው ንዑስ ርዕስ ውስጥ ስለተጠቀሰ ወደ ኋላ መለስ ብሎ መመልከት ይሻላል::

**በ. የዲያቆን ሞጣሕት:-** ሞጣሕት በቀሚስ ላይ የሚጠለቅ ሆኖ በአሁኑ ዘመን ከሁሉ ቦታ የተለመደ አይደለም፤
ነገር ግን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ እንዳሉ አንዳንድ ፀሐፍት ይጠቁማሉ::
ሞጣሕት በሚጠቀሙ ጊዜ ዋናው ዲያቆን ከረዳቱ ለመለየት የመስቀል ቅርጽ ያለበት ጨርቅ /ቀሚስ/ ሙሉ ዲያቆን የቀኝ እጁን አውጥቶ ያጣፋዋል፤ ረዳት ዲያቆን ግን ሳያጣፋው እንዲሁ ያደርጋል:: ሙሉ ያለመሆኑን ለማመልከት ነው::

**ተ. አክሊል:-** ከመልካም ጨርቅ የሚሰፉ ክብና መሐሉ ላይ መስቀል ያለበት ሆኖ ይዘጋጃል::

«ሃይማኖቴን ጠብቂያለሁ መልካሙን ገደል ተጋድያለሁ የድል አክሊል ይጠብቀኛል»2ኛ ጢሞ 4÷7-8
በታላላቅ አድባራትና ገዳማት ዲያቆኑ አክሊል ያደርጋል:: በአሁኑ ዘመን አልፎ አልፎ አክሊል የመሰለ እንደቆሱ ቆብ አድርጎ ይቀድሳል::

**ምሥጢሩ:-** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ አይሁድ በራሱ ላይ የደፉበት የሾህ አክሊል ምሳሌ ነው::

ልብስ ተክህኖ ባጠቃላይ በክብርና በንጽህና በቤተክርስቲያ ዕቃ ቤት ሊቀመጥ ይገባል:: ከዚህ ውጭ በተፈለገ ቦታ ሊቀመጥ አልተፈቀደም::





የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

ዘጸ 29÷6 መዝ 20÷3 ማቴ 27÷29 1ሳሙ 22÷18 ዘጸ 28÷40-42
ዘሌ 8÷9 ሰቆ 5÷16 2ጢሞ 4÷8 ማር 15÷17 ዘጸ 39÷29
ዘካ 6÷11 ራእ 2÷10-11 መሳ 14÷12 ማቴ 34
ዘጸ 28÷3-39 ዘጸ 31÷10-11 ሕዝ 44÷17-19 ምሳ 31÷22





www.ethiopianorthodox.org

## 2. ልብሰ ታቦት

ከመልካ መልካም ጨርቅ የሚዘጋጅ ጌጥና ዘርፍ የተበጀለት ነው:: ታቦት የሚከብርበትና የሚጎናፀፈው ነው::

**ሀ. መጎናጸፊያ:-** መንበሩ የሚለብሰው ሆኖ ታቦት በክብረ በዓል ጊዜ ሲወጣ የሚጎናጸፈው ነው::

**ለ. ቀጸላ:-** ታቦቱ መጎናጸፊያውን ከተጎናጸፈ /ከለበሰ/ በኋላ ከላይ የሚደረብ ባለጌጥ ዘርፈ ልብስ ነው::

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

1ኛነገ 21÷38-41 ኢሳ 3÷19 ራእ 12÷3 ባሮ 5÷2

## 3. መጋረጃ /መንጦላዕት/

ከጥሩ ጨርቅ መልከኛ ሆኖ ተዘጋጅቶ በሦስቱም የመቅደስ በር የሚደረጉ መጋረጃዎች ናቸው:: አገልግሎቱም ለመቅደሱ ክብር የሚሰጡ ናቸው::

**አጠቃቀሙ:-** በቅዳሴ ጊዜ መሥዋዕቱን ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ይዘው ከገቡ በኋላ ይዘጋል፤ አሐዱ አብ እንደተባለ ዲያቆኑ ስግዱ ብሎ ከፍትሐት ዘወልድ አስቀድሞ ይከፈታል አንደኛው ዲያቆን «ይህን የካህኑን ቃል ያቃለለ የሳቀና የተነጋገረ. . . » ሲል ይዘጋል፤ ሁለተኛው ዲያቆን «መኳንንት ሆይ በሮቻችሁን ክፈቱ» ሲል ይከፍታል፤ ዲያቆኑ «በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ» ብሎ ከዚያም «ለጸሎት ተነሡ» ካለ በኋላ ካህኑ «ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» እንዳለ ይዘጋል::
«ጸልዩ በእንቲአነ» ለማለት ሲወጣ ይከፈታል ካህኑ «ነዳፌ ነፍስ...» የሚለውን ጸሎት ሲጨርስ ይዘጋል ዲያቆኑ «አድኅኑ» ከማለቱ በፊት ይከፈታል::





**ምሥጢሩ:-** መጋረጃ የኪሩቤል ምሳሌ ነው::
መጋረጃ ለሁለት የተከፈለ መሆኑ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ከላይ እስከታች የተከፈለበት ምሳሌ ነው:: /የሥጋና የነፍስ ምሳሌ ነው::/

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 26÷7-10 | ዘጸ 38÷9-20 | ዕብ 6÷19 |
| ዘጸ 26÷31-34 | ማቴ 27÷51 | ዕብ 10÷20 |
| ዘጸ 36÷35-38 | የሐ ሥራ 10÷11 | የሐ ሥራ 11÷5 |

## 4. ምንጣፍ

ልብስ ከሚዘጋጅበት ክርና ሸማ የሚዘጋጅ የወለል ላይ ልብስ ወይም ለተከረው ነገር መረገጫና መረማመጃ ነው:: ለወንበርም ምንጣፍ ይዘጋጃል::

ለወለልና ለመቀመጫ የሚዘጋጀው ምንጣፍ ምንም ዓይነት ሥዕል ሊኖረው አይገባም:: ምናልባት የንዋየ ቅድሳት ሥዕል ወይም የቅዱሳን ጻድቃን ሥዕል ቢኖረው በግድግዳ ላይ አድርጎ በክብር ማስቀመጥ እንጂ በወለል ላይ እንዲረገጥ መሆን የለበትም:: ከዚህ ውጭ ልሙጥ ምንጣፍ በወለል መቀመጫ ላይ ሊደረግ ይችላል::

**ምሥጢሩ:-** በሆሣዕና ዕለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያና በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ሲሔድ የዘንባባ ዝንጣፊና የለበሱትን ልብስ ለክብሩ ሲሉ ያነጠፉትን ለማስታወስ ነው::

ሌላው ደግሞ:-
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንቅፋትና እሾህ እንዳያገኛቸው የብርሃን ደመና አንጥፎ መምራቱ ሚያስታውሰን ነው::




www.ethiopianorthodox.org

## 5.ድባብና ጥላ /ጸላል/

ዘንጉ ከወርቅ ከብርና ከብረት ከእንጨት ሊሠራ ይችላል ጨርቁ ከከበረ ነገር ሆኖ ወርቃማ ቀለም ያለው መርገፉ የወርቅ ወይም የብር የሚዘረጋ /ሚወጠር/ ነው። ተ ሕዋስያንንም ይከላከላል።

ታቦት በሚከብርበት ጊዜ ጥላ ይዘረጋል። በቅዳሴ ጊዜ ጥላ አገልግሎት አለው። ይኸውም ወንጌል ሲነበብ ቅዱስ ቁርባን ከቤተልሔም ሲመጣ መስቀሉን ይዘው ለማዕጠንት ሲወጡ በአጠቃላይ ክቡር የሆነ ነገር የሚጠለልበት ነው።

<u>ምሥጢሩ፡-</u> ሙሴ የኪዳኑን ታቦት ሲቀበል የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው።








## 6. ግምጃ

ከልዩ ልዩ ሐርና ወርቅ ዘቦ የሚሠራ ወይም የሚቀለም ልብስ /በፍታ/ አገልግሎቱ ለቅዱሳት መጻሕፍት መሸፈኛና ለሌሎች ንዋያተ ቅድሳት ልብስ ያገለግላል፤ ባለጌጥ ከጠፋ ይሄው ግምጃ መጋረጃ ይሆናል።

« ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ ትለብሳለች» ምሳ 31÷22

## 7. ማህደር

ከቆዳ የሚሠራ የቅዱሳት መጻሕፍት መክተቻ፣ ማኖሪያ፣ ማሳደሪያ ነው፤ ሲዘጋጅ አጠቃላይ ሽፋኑና ማንገቻው ከቆዳ መሆን አለበት። ቢቻል መስፊያውም የቆዳ ገመድ ቢሆን መልካም ነው። ካልሆነ በጅማት ይሠፋል።

<u>ምሥጢሩ፡-</u> ማህደር የእመቤታችን ምሳሌ ነው።





www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስድስት

## ዜማ ዕቃዎች

የዜማ ዕቃዎች የሚባሉትን ከመዘርዘራችን በፊት ስለዚህ ቃል /የዜማ ዕቃዎች/ ሙሉ ትርጉምና ፍቺ እንዲሁም አገልግሎት እንመለከታለን:-

ዜማ ማለት ስልት ያለው ጩኸት ማለት ሲሆን ድምጽ እና የሠዎች ዜማ በ 3 ይመደባል ግዕዝ ዕዝልና አራራይ የዜማ ዕቃዎች ማለት በስልት የሚዜምባቸው ዕቃዎች በገና፣ ከበሮ ፣መሠንቆ፣ጸናጽልና ሌሎችም ናቸው:: ዳዊትና ሌሎች ነገሥታት በእግዚአብሔር ቤት እንዲያመሠግኑበት ሆነ /1ኛ ዜና 6÷31-32 2ዜና 29÷25-26 ነህ 12÷46

ዳዊት ብዙ መዘምራንን በዜማ ዕቃ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ አዘጋጀ 1ዜና 15÷16

በአዲስ ኪዳን ካህናትና ምዕመናን በከበሮ በጸናጽል እንዲዘምሩ ቅዱስ ያሬድ አሳይቷል::

### የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| 1ዜና 6÷31 | ኢሳ 6÷20 | 1ሳሙ 16÷16-23 |
| ነህ 12÷46 | 2ዜና 5÷12 | 1ዜና 13÷8 |
| ዘጸ 15÷20-21 | መዝ 149÷3 | ኤፌ 5÷19 |
| 2ዜና 29÷25-26 | 1ሳሙ 18÷6 | ቆላ 3÷16 |
| መዝ 150÷6 | 2ሳሙ 6÷5 | ዘፍ 31÷27 |
| 1ዜና 15÷16 | መዝ 91÷3 | 1ቆሮ 14÷26 |
| | መዝ 32÷2 | ዕዝ 2÷65 |






## የዜማ ዕቃዎች በሦስት ይከፈላሉ

ዘማሪው በእጁ የሚከረክራቸው ወይም በመከርከሪያ የሚመታው በገናና መሰንቆ::የሚነፉ የዜማ ዕቃዎች መለከት እምቢልታ ዋሽንት::ዕቃዎቹ እርስ በርስ ማማታትና በእጅ በመምታት የሚጠቀምባቸው የዜማ ዕቃዎች ከበሮ፤አታሞ ነጋሪትና ጸናጽል ናቸው::

**1. በገና:-** ከእንጨት የሚዘጋጅ ሆኖ ክሩ ከጅማት ይበጃል:: አሥር አውታር ያለው በገና ይባላል፤ ይህም ዓቢይ የዜማ ዕ ቃ ነው:: በገና ሲዘጋጅ ቁመቱ የረዘመ ሆዱ የሰፋ መሆን ይኖርበታል::





www.ethiopianorthodox.org

<u>ምሥጢሩ፡-</u> በገና የእመቤታችን ምሳሌ ነው፤
-ሰዛው የእመቤታችን ምልጃዋና ፍቅሯ ነው፤
-አሥር አውታር የአሥርቱ ቃላተ ኦሪት ምሳሌ ነው፤
-ግራና ቀኝ ያሉት ሁለት ዓምዶች የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ እግዚአብሔር ምሳሌዎች ናቸው::
በተጨማሪም ሁለቱ ዓምዶች በብሉይና በሐዲስ ይመሰላሉ::
-ከእንጨት መሠራቱ ጌታችን በእንጨት መስቀል መሰቀሉን
-የበገና ትልቅና ግዙፍነት እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሞላ /ምሉዕ በኩለሄ/ መሆኑን ያመለክታል::

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ 31÷27 | ዳን 3÷15 | ራእ 5÷8 | ዳን 3÷10 መዝ 150÷3 |
| ዘፍ 4÷21 | 2ሳሙ 6÷5 | ራእ 14÷2 | መዝ 32÷2 |
| 2ዜና 29÷25 | 1ሳሙ 16÷16-23 | 2ዜና 5÷12 | 1ዜና 15÷21 |
| ኢሳ 5÷12 | 2ዜና 20÷28 | ሰቆ 5÷14 | መዝ 91÷3 |
| 1ዜና 13÷8 | ሚሬ 40÷21 | 1ዜና 15÷16 | ዳን 3÷5 |







**2. <u>መሰንቆ፡-</u>** መሰንቆ አንድ ምሰሶና አንድ ክር ያለው የዜማ ዕቃ ነው:: ክሩ ከፈረስ ጭራ ይዘጋጃል በአንድነት የሚወጠረው ክር ብዛቱ ቢያንስ አርባ ቢበዛ ሰማንያ ይሆናል:: ለእግዚአብሔር ክብር ይዘመርበታል::

<u>ምሥጢሩ፡-</u> መሰንቆ የእመቤታችን ምሳሌ ነው::
-አንድ ምሰሶ መኖሩ ሃይማኖት አንድ መሆኗን ፤
-ክሩ አንድ ወራጅ መሆኑ አንዲት ጥምቀት ፤
-የክሩ ጥቅል ብዛት ቢያንስ አርባ መሆኑ ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀናቸው ጥምቀት ማግኘታቸው፤ ቢበዛ ሰማንያ መሆኑ ሴቶች በተወለዱ በሰማንያ ቀናቸው ጥምቀት ማግኘታቸውን ነው::
-ክሩ ዕጣን እየተቀባ ይዘመርበታል፤ ይህም ዕጣን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሲሆን ክሩ የጥምቀት ሆኖ በመጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደሚገኝ ያመለክታል::
-መሰንቆ አምስት ያህል መሰቀል ይታይበታል


ሀ. የምሰሶ አናት ላይ
ለ. መቃኛው ከምሰሶ ጋር ሲተያይ
ሐ. የመሰንቆ ሳጥን ቅርጽ
መ. የክር መወጠሪያ በርኩማ ከክር ጋር ተመሳቅሎ ሲታይ
ሠ. መከርከሪያው በመሰንቆ ክር ጋር እልፎ ሲከረከር፤ አምስት መስቀል መታየቱ አምስቱ ቅንዋተ መስቀል ያስታውሰናል::

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 2ዜና 29÷25 | መዝ 32÷2 | ዳን 3÷5 |
| መዝ 91÷3 | ዳን 3÷10 | መዝ 150÷3 |
| ዳን 3÷15 | መዝ 149÷3 | 1ዜና 15÷16 |
| ሚሬ 40÷21 | 2ዜና 5÷12 | 2ዜና 20÷28 |
| 1ዜና 13÷8 | 2ሳሙ 6÷5 | ኢሳ 5÷12 |



www.ethiopianorthodox.org









**3.እምቢልታ:-** ከቀርከሃና ከቱቦ መሠል ነገር የሚዘጋጅ የዜማ ዕቃ ነው። እንደዋሽንት የመሰለ ሆኖ በመጠን ትልቅ የሆነ ሲሆን ታቦት ሲወጣ /ሲከብር/ ይዘመርበታል፤ እንዲሁም ነገሥታት ግብር ሲያገቡ የሚያስነሱት፤ ዳዊትም መዝሙር በእምቢልታ ይዘምር ነበር።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>


መዝ 150÷4 ዳን 3÷15 ማቴ 9÷23 ኢዮብ 30÷31
1ዜና 15÷28 ኢሳ 5÷12 ዳን 3÷10 ኢዮብ 21÷12 ዳን 3÷5



**4.መለከት:-** ከከብት ቀንድ ከብረትና ከሌላም ብረት ነክ ነገር ሊሠራ ይችላል። ለአዋጅ መንገሪያና ለመዝሙር ያገለግላል። መለከት ብዙውን ጊዜ ከቀንድ ይሠራል።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>

2ሳሙ 6÷15 ዘኍ 10÷1-10 2ዜና 20÷28 ዳን 3÷15
1ዜና 15÷28 2ዜና 5÷12-13 ማቴ 24÷31 ዳን 3÷10
ዘፍ 4÷21 ዳን 3÷5 ኢያሱ 6÷20





www.ethiopianorthodox.org

**5. ዋሽንት:-** ከሸንበቆ ወይም ከቀጭን ቀርከሃ ከብረትም ሊሠራ የሚችል የዜማ ዕቃ ነው።
ዋሽንት አራት ቀዳዳዎች አሉት።

ምሥጢሩ :-አራት ቀዳዳዎች በአራቱ ወንጌላዊያን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ሉቃስ፣ዮሐንስ ይመሰላሉ።ዳን3÷5 ዳን3÷10 ዳን 3÷15




**6. ከበሮ:-** ከእንጨት ተዘጋጅቶ በጠፍርና በቆዳ የሚለጎም /ንዋየ ማህሌት/ ነው።
ለክብረ በዓል በበዓለ ንግሥ ዕለት ለእግዚአብሔር ክብር የሚመታ የሚዘመርበት ነው።

ምሥጢሩ:- አፉ ሁለት ነው፤ ሰፊና ጠባብ። ሰፊው ምሉዕ በኩለሄ /እግዚአብሔር በሁሉ ሙሉ መሆኑን/ ጠባቡ ደግሞ ወልድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑንየሚያመለክት ነው።
-ከበሮ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ይመሠላል፤
-እንጨቱ ከቆዳ ጋር የተለጎመበት ጠፍር ጌታችን አይሁድ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ጊዜ በጅራፍ ሲገርፉት በገላው ላይ ይታይ የነበረው ሰንበር ይመሰላል።
-ከበሮውን የሚሸከሙበት ገመድ የተገረፈበት ጅራፍ ምሳሌ ነው።
-ከበሮ የሚለብሰው ሱቱ ጌታችን የለበሰው ቀይ ግምጃ ምሳሌ ነው







## የከበሮ አመታት ምሥጢር

መጀመሪያ ከበሮ ተቀምጦ ነው የሚመታው፤ ሲመታም ቀስ በቀስ እየተባለ ነው። በመሬት መመታቱ ጌታችንን አይሁድ በመሬት እየጎተቱ መምታታቸውን በግራና በቀኝ ሲመታ/ከፊሉ በግራ ቀሪው በቀኝ ከወዲያ ሲመታ ወዲህ ሲያዘነብል ከወዲያ ያለው ሲመታ የነበረውን ለማስታወስ ነው።
-ከበሮ በትከሻ ተደርጎ ሲመታ ከወደቀበት እንሥተው እንደመቱት።
በመጨረሻም በፍጥነት ሲመታ ጌታችን ሊሰቀል ሲቃረብ በፍጥነት መምታታቸውን ያስታውሰናል።


### የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

| | | |
|---|---|---|
| መዝ 150÷4 | 1ሳሙ 18÷6 | ዘፍ 31÷27 |
| ዘጸ 15÷20-21 | 2ሳሙ 6÷5 | ኢሳ 5÷12 |
| መዝ 149÷3 | 1ዜና 13÷8 | |



www.ethiopianorthodox.org

**7.ጸናጽል:-**ከብርና ከነሐስ ከሌላም ብረት የሚሰራ:: እንዲሿሿ የብረት ቅጠል ይደረግበታል አገልግሎቱም ለእግዚአብሔር ክብር ይዘመርበታል፤ ጸናጽል ከከበሮ ጋር አብሮ የሚሄድ የዜማ ዕቃ ነው::





ምሥጢሩ:- በግራና ቀኝ ያለው ዓምድ የብሉይና የሐዲስ ምሳሌ
-በሁለቱ ዓምዶች መሐል ያሉት ሁለቱ ቀጫጭን ዘንጎች ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያያት መሠላል ምሳሌ ሆኖ::
-በዘንጎቹ ላይ ያሉት የብረት ቅጠሎች ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በመሠላል ላይ ሲወጡ ሲወርዱ ያያቸው መላእክት ምሳሌ ነው::





በሌላም በኩል የብረት ቅጠሎቹ ብዛት ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት ይሆናል:: አምስት ሲሆን የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ሰባት ቢሆን ደግሞ በሰባቱ ሰማያት::
-የብረት ቅጠሎቹ በመጀመሪያ ዘንግ ላይ ሁለት ይሆናሉ፤ ይህም ወልድ ሁለት ልደት ቅድመዓለም ያለ እናት ከአብና
-ኋላም አዳምን ለማዳን ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ፤
-በሁለተኛ ዘንግ ላይ ሦስት ሲሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል::
-ድምጹ ያማረና መልካም መሆኑ በመላዕክት ዜማ ይመሰላል::
-ወዲያና ወዲህ መባሉ የጌታችን በአይሁድ መንገላታት ምሳሌ ነው::



<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ</u>


2ዜና 29÷25 2ዜና 512 1ቆሮ 13÷1-2
መዝ 150÷5 2ሳሙ 6÷5 1ዜና 13÷8 1ዜና 15÷16



www.ethiopianorthodox.org

8. **<u>አታሞ፡-</u>** ከእንጨትና ከቆዳ የሚዘጋጅ እንደ ከበሮና ነጋሪት በእጅ የሚመታ ባለ አንድ አፍ የዜማ ዕቃ ነው፡፡ ይህ የዜማ ዕቃ በዚህ ዘመን ተጠቃሚ የለውም፡፡ «እንዲህም ሆነ ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ እየዘመሩና እየዘፈኑ እልልም እያሉ ከበሮና አታሞ ይዘው ንጉሡን ሳኦልን ሲቀበሉ ሴቶች ከእሥራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ»1ኛ ሳሙ 18÷6

«እነሆም የሴሎ ሴቶች ልጆች አታሞ ይዘው ለዘፈን ሲወጡ ከወይኑ ስፍራ ወጡ» መሳ 21÷21








9. **<u>ነጋሪት፡-</u>** ከእንጨትና ከቆዳ የሚሠራ ባለ አንድ አፍ የዜማ ዕቃ ነው፡፡ ይህ የዜማ ዕቃ ከአታሞ ጋር ይመሳሰላል አገልግሎቱ መልእክት ለማስተላለፍና ለክብረ በዓል ማድመቂያ ነው፡፡

«ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆም በከበሮም በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር» 2ሳሙ 6÷5

«በዳግም ምጽአት /ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ/ ለፍርድ ሲመጣ የሚመታ» ዮሐንስ ራእይ

<u>ምሥጢሩ</u>፡- የነጋሪት ድምጽ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያሳስባል፡፡





www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## ቅዱሳት ሥዕላት

ቅዱሳት ሥዕላት የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ናቸው:: ቅዱሳት ሥዕላት የሚባሉት የቅድስት ሥላሴ፣ጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእመቤታችን ቅዱስት ድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላዕክት፣ የነቢያትና ሐዋርያት የጻድቃንና ሰማእታት ሥዕላት ናቸው::

የቅዱሳን ሥዕላት በጥንት ዘመን የሚያዘጋጁት ድንጋይና እንጨት ጠርበው ቆዳ ፍቀው ከአፈር ቀለም በጥብጠው ነበር በዚህ ዘመን ግን ቴክኖሎጂ ባመጣው መሳሪያ የጥንቶችን ፎቶ በማንሳት ፎቶ ኮፒ በማድረግ ወይም በማባገር ማሽን በማራባት ነው:: እንዲሁም በዘመኑ ሠዓሊያን በሸራ በቆርቆሮ በክርታስና በመሳሰሉት እየተሳሉ ይቀርባሉ::

የቅዱሳንን ሥዕል ለመሳል ወይም ለማሳል በቅድሚያ የሚሳልበት ነገር ቢመረጥ መልካም ነው:: ይኸውም ሥዕሉ በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይፈገፍና እንዳይለቅ የሚሳልበት ቀለም ጥራቱን የጠበቀና መሳያው ጠንካራ መሆን፤ እንዲሁም ሠዓሊው ልዩ ዕውቀት /በቤተክርስቲያን የታነጸ/ መሆን ይኖርበታል::

ሥዕሉ ከትውልዱ ትውልዱ እንዲተላለፍና ለሥዕሉ ባለቤት ክብር ጭምር ነው::





## የቅዱሳት ሥዕላት አጠቃቀም

የቅዱሳንን ሥዕል በክብር ማስቀመጥ ቅዱሳኑን ማክበር ነውና በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባው ሥዕል የሥላሴ የኢየሱስ ክርስቶስ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ጽላቱ የተቀረጸት መልአክ ወይም ጻድቅ ሥዕል ነው:: የሚቻል ከሆነ ግን ማንኛውም ቅዱሳት ሥዕላት ቢኖሩ መልካም ነው::

በቤተክርስቲያን ዙሪያ ግድግዳ ላይ የሚሰቀሉት የሚለጠፉት ወይም የሚሳሉት ቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎታቸው ምዕመናንም ሆኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሥዕሉ ፊት ሆነው ወደ ፈጣሪ ጸሎትና ተማፅኖ ማቅረቢያ ነው::

ከሥዕል ፊት ሆኖ መጸለይ ለሥዕሉ ባለቤት ለምሳሌ የጌታ ሥዕል ከሆነ ለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእመቤታችን ከሆነም ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የመላእክት አሊያም የጻድቃን ከሆነም ለመላእክቱ ወይም ጻድቃኑ ክብር ነው::

ይሆንልኛል ይደረግልኛል ብሎ በንጹህ ህሊና በቅን ልቦና ቢጸልይ ይሆንለታል ይደረግለታል::

በመኖሪያ ቤታችን ቅዱሳት ሥዕላትን ስናስቀምጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፤ ይኸውም የምንሰቅልበት ቦታ ከቆሻሻ የጸዳ ክፍሉ /ቤቱ/ ጸያፍ ነገር የማይሰራበት መሆን አለበት::



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱሳት ሥዕላት በየጊዜው ዕጣን ልናጤስባቸው ይገባል:: የቤተሰብ እና የግል ጸሎት በምናደርግ ጊዜም በሥዕሉ ፊት ሆነን ልንጸልይ ይገባል::

ሌላው ደግሞ ከቅዱሳት ሥዕላት አጠገበ አለማዊ ወይም የማይስማማ (መጥፎ መልዕክት የሚያስተላልፍ ሥዕል) ማኖር አይገባም::

ለዚህ ርዕስ በቂ የሆነ ትምህርት ለማግኘት «ቅዱሳን ሥዕ ላት አመጣጥና ታሪክ ከትምህተ ሃማኖት ጋር» የሚል መጽሐፍ ብታነቡ መልካም ነው::







# ምዕራፍ ስምንት

## ዕቃ ቤት /ንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ/

ዕቃ ቤት የሚባለው የቤተ መቅደስ ዕቃዎች /ንዋየ ቅድሳት/ ማስቀመጫ ቤት ነው:: ሕዝ 42÷2 ነገ.10÷22

ንዋየ ቅድሳት የተከበሩ የቤተ እግዚአብሔር ወይም የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ዕቃዎች ስለመሆኑ በንጽህና ሊቀመጡ ይገባል:: ስለዚህ ለእነኚህ ዕቃዎች ማስቀመጫ ዕቃ ቤት ሊዘጋጅ ግድ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት ስለ ዕቃ ቤት ተጽፏል:: ሕዝ 42÷1-14 ይመልከቱ::

## የንዋየ ቅድሳት መደርደሪያና ሣጥን

ለንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ሳጥንና መደርደሪያ ማበጀት እጅግ በጣም ወሳኝ ከመሆኑም በላይ ትዕዛዝም ነው::

ይህም መዘጋጀቱ ንዋየ ቅድሳት ከብዙ አደጋ መከላከል ያስችላል ለምሳሌ:-

- ከዝናብና ከፍሳሽ ፤ከአቧራ ፤ከዘራፊና ቀማኛ ወዘተ. . .

መደርደሪያውና ሳጥኑ ከብረት የተዘጋጀ ቢሆን በጣም ጥሩ ነው:: የማይቻል ከሆነ ግን ነቀዝና ብል ምስጥም ከማይበላው እንጨት ቢሰራ መልካም ነው::

ይህም ከሆነ በኋላ ብዙን ጊዜ የማንጠቀምባቸው ወይም በትርፍነት የተቀመጡ ንዋየ ቅድሳትን ለምሳሌ ጥላ የዜማ ዕ ቃዎች አጠቃላይ አልባሳትና ሌሎችም በየጊዜው መናፈስ መወልወልና መታጠብ አለባቸው::



www.ethiopianorthodox.org

# መልካም ስጦታ

ከ.......................................


ቀን.......................................

ፊርማ.......................................

ለ.......................................

.......................................

## የኢትዮጵያ ቅርሶች ጥበቃ ክብርና እንክብካቤ ይደረግላቸው፤ ከቱሪዝም ባሻገር የመንፈስ ምግብ ናቸው።




www.ethiopianorthodox.org